በአብዮት አደባባይ ካሰማው ቧልት በስተቀር/ አሁንም "ለተራበው ጥይት ስጠው" የሚል ፋሽስታዊና ኢሰብአዊ መልስ ነው። በአጭሩ ቢጠማዘዙት ቢሸላልሙት የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት አዋጅ የኢትዮጵያን ውድቀትና ጥፋት ማባባሻ አዋጅ ከመሆን አያመልጥም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፋሽስቶቹ ከጨካኝነት የፅልመት አገዛዝ፣ ሽብር ከእልቂትና ከጠርነት ለመገላገል አሁንም ያለው ዋና አማራጭ ሕዝባዊ ገድሉን ማፋፋም ነው። ለመብቱ፣ ለነፃነቱ፣ ለራሱ ደህንነትና ለሰላምና ክብር፣ ከረሀብ፣ ከድርቀትና ከመከራ ለመላቀቅ ገድሉ ግድ የሚለውን ህብረት በመመስረት አስፈላጊውን መስዋዕትነት በቁርጥነት በመክፈል ዓለም የመሰከረለትን የቁርጥ ተጋድሎ ታሪክ በማረጋገጥ ከመታገል ሌላ መፍትሔ የለውም።

የፋሺስቶች የእልቂት አዋጅ በሕዝባዊ ገድል ይከሸፋል!!

ሞት ለፋሺስቱ መንግሥትና ለሶቭየት ሶሻል ኢምፔሪያሊዝም!!

እናቸንፋለን!!!